# የትጥቅ ትግል

***መግቢያ***

***የሀገራትና የመንግሥታት ጦር ሠራዊት የአመሰራረትና የአደረጃጀት ህግና ደንብን ተከትሎ እንደሚቋቋመው ሁሉ የጎሬላ /የሽምቅ/ተዋጊም የራሱ የሆነ መርህ /ፕሪንስፐል/ያለው ከመጀመሪያ እስከ ሦስተኛ እርከን ድረስ እድገትና ህግጋቱን ጠብቆ የሚያድግ በየደረጃው ሊወጣ የሚችልው የግዳጅ አፈፃፀ መመሪያዎች ያሉት በሽምቅ ውጊያ አጠቃቅ ጥበብና ዶክትሪን የሚመራ እራሱን በሁለት ሥልታዊ ክፍሎች በመክፈል የሚገለጥ ሌላኛው የጦርነትና የትግል አካሄድ እስት ራቴጅ ነው:: ይህንን አማራጭ መንገድ በመከተል በአለማችን የተለያዩ ዓላማና ግብ ያላቸው የትጥቅ ትግሎች ቀደም ባሉጊዜያትና አሁንመ እየተካሄዱ ሲሆን የጠመንጃ አመፆቹ ምክንያትና መንሴአቸው .1ኛ.ከወራሪዎችና ተስፋፍዎች ነፃ ለመውጣት .2ኛ. የተነሱበትን ዓላማና ግብ እየሳቱ በመጨረሻ ከታገሉት አንባገነን መንግሥት በልጠውና ተክተው ቢገኙም የትግል አነሳሳቸው የጨቋኝ ስርአትን አስወግዶ የሕዝብ ሥልጣንን ለማስፈን የተደረጉ .3ኛ.ከቀኝ ግዛት ፍፃሜ ማግስት በጭቆና .በዲሞክራሲና .በነፃነት.ስም ጎጠኝነት በመደረብ ለጠባብ አመለካከትና ዓላማ ሉዐላዊን ሀገርና ሕዝብ በማዳከም ለውጪ ኃይሎች ፍላጎት በመሣሪያነት ማገልገል ሲሆኑ.እነዚህ ፊልማያዎች እንደየ ሕዝቦቹና የአካባቢው ሁኔታ ከሁለቱ አይነት የሽምቅ አደርጃጀት እንደየ ምርጫቸው በተግባር ላይ የዋሉ .ሀ.ጥምር የጎሬላ ውጊያ ሥልት ..ለ.ሀገር በቀል የሽምቅ ውጊያ ሥልት ናቸው***

## ጥምር የጎሬላ ውግያ

***የራሱን ዓላማና የአስታጣቂ ባዕዳንን ፍላጎትና ጥቅም ከጠመንጃው ጋር ተሸክሞ በጥቂቱ ያሰባሰበውን የጎሬላ ተዋጊ ከፍት በማስቀደም በአጎራባች/በሌላ/ አገር የጦር ኃይል እየተረዳ ከውጪ ወደ ውስጥ የሚያደርገው ውጊያ ሁለቱንም አይነት ተዋጊዎችን ማለት መደበኛውን ሠራዊትና.የጎሬላ ተዋጊውን በመያዙ ጥምር የሽምቅ ተዋጊ የሚለውን ስም እንዲይዝ አድርጎታል::***

## ሀገር በቀል የሽምቅ ውጊያ

***የዚህ አይነቱ ሽ.ተዋጊ እምነቱን በወገኖቹ ላይ አድርጎ የሀገሩን.ጋራና.ሽንተረር..በተገንነት ተማምኖ ከገጠር እስከ ከተማ በዜጎች ሁለገብ ድጋፍ የሚስጥው መሰረቱን በሕዝብ ላይ የጣለ በሀገር ውስጥ የሚደራጅ ሀገር በቀል የትግል ኃይል ነው..ድንገት የተረሳ ነገር ካለ በመጠኑም ቢሆን አንባቢን ካስታወስኩ ወደ ተነሳሁበት ጉዳይ ስገባ..ረዘም ካሉ ጊዚያት ጀምሮ ከአስመራ ስለሚንደረደረው ጦርና እስከ አሁኑ.ምታ ነጋሪት.ክተት..ሠራዊት.ድረስ ብዙ የጦርነት ወሬዎችን ስንሰማ ቆይተናል ግን ከፕሮፓጋንዳው ባሻገር የተያዘው መንገድና የጦርነት አዋጅ ከጎሬላ አደረጃጀትና ዶክትሪን አኳያ ነፃ ሊያወጣን ስለ መቻሉ አቅም እንደፈቀደ የጠመንጃን አመፅ ምንነት ከሥልት አንፃር ለማሳየት ስሞክር::***

## 1ኛ የጦርነት አዋጁን...ከጥምር የሽምቅ ውጊያ አንፃር

***በዚህ መንገድ በትጥቅ ለመታገል የመረጠው ኃይል በሥልቱ አካሄድና ባህሪ ከሌላ አገር በመነሳት ከውጪ ወደ ውስጥ ጥቃት ማድረስ ይቻለው ዘንድ በቅድሚያ መነሻ. መቃረቢያና መሸሎኪያ ይሆናሉ ተብለው የሚገመቱ የአጎራባች ሀገራትን ወቅታዊ ሁኔትን በሚገባ የማየትና የማወቁ ጉዳይ ለመታገል የወሰነው ክፍል የሀ ልውናው መሰረት ብቻ ሳይሆን ውጤት ማመጣት መቻልና አልመቻሉን መልስ ለማግኘት የሚጠቅም ነጥብ በመሆኑ የአካባቢውን ገፅታ ማየቱ የግድ ይሆናል ሱዳን.ከጥንቱ የጨካ ጓደኝነታቸው ባሸገር ወያኔ ቤተመንግስቱን ከተቆጣጠረ በኋላ..ከሱዳን. ጋር ብዙ ውሎችን የተፈራረመ ቢሆንም በዋንኛነት በሁለቱም ወገን ለተቃዋሚዎች ቦታና ጥገኝነት አለመስጠት .የአፍሪካ ሕብረት ያፀደቀውን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ያለው የሀገሮች ድንበር ባለበት የፀናና የረጋ ይሆናል የሚለውን ህግ በመጣስ ከሱዳን ጋር የድንበር መካለል ውል እንዲደረግ በመፍቀድ ተቃዋሚ ኃይል መተላለፍያ መንገድ እንዳያገኝ .የሱዳን ጦር የኢትዮጵያን ወሰን ጥሶ እንዲወርና እንዲሰፍር በማድረግ መለስ መሬታችንን ሸጠ መጠጊያ ቀዳዳውን ያሳጠረ በመሆኑ በዚያች ሀገር በኩል ያለው ዕድል የተዘጋና***

ለሚከተው ሠራዊት ምቹ ሁኔታና ተስፋ የሌለው መሆኑን ያረጋግጣ ጅቡቲ ወያኔን በሚደግፉ መንግሥታት መዳፍ ውስጥ ያለችና እራሷን ለማኖር የምግብ ፍጆታዋን ከድሬ ደዋ ባቡር መግባትና ህልውናዋን ከኢትዮጵያ ጋር ያቆራኘች የወደብ ኪራይ ተጠቃሚዋ ትንሿ ጎረቤት ከኢሳያስ ዐይኖች ጋር ሚጥሚጣ የተቃባችና ከመለስ ጋር ወዳጅነት የመሰረተች በመሆኗ ባላቸው ግንኙነት ሳቢያ መቆናጠጫ መሬትና መነሻ መስመሮቹ ይተዘጉ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን .ሀገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት የምትልካቸውና ለመሰረታዊ ፍላጎት የሚውሉ ፍጆታዋን የምታስገባበት የሕይወት መስመር በመሆኑ. በሻቢያም ሆነ.በሌላ ጎይል ተዘግቶ ጉሮሮው እንዳይታነቅ የወያኔ የመከላከያ መሥሪያቤት.በእስትራቴጂካል ዕቅዱ .በዋንኛነት ትኩረት ሰጥቶ የሚከታተለውና የሚጠብቀው ከህልውና አንፃር አንዱ የስጋት አቅጣጫው በመሆኑ በዚያ ያለው ምቹትና ህልም ውጤቱ ትልቅ ዜሮ እንዲሆን ያሌው ተጨባጩ እውኔታ ያስገድደዋል::

ኤርትራ..ክሌሎች ሀገሮች በአንፃራዊ መልኩ በአማራጭነት የወቅቱ ሁኔታ የፈቀደውና ይሆናል ተብሎ የሚገመተው የመምጫና የመቃረቢያ አቅጣጫ አጎራባች ሀገር ኤርትራ ናት.ይህ ከባሕረ ነጋሽ መሬት ላይ ተንደርድሮ የሚነሳው የክተት ጦር ወደ ውስጥ በጥልቀት መግባት ይቻለው ዘንድ ሻቢያ የጀርባ ዕርዳታና ድጋፍ በመስጠት ለተነሳበት ዓላማ ለማብቃት.በግንባር መስመር ላይ መሽጎ የሚጠብቀውንና በተጠባባቂነት የተሰለፈውን ጠቅላላ .ከ300.000 - 400. 000 የሚገመተውን የወያኔን ሠራዊት በሚገባ ቀጥቅጦና ደምስሶ ለዘማቹ ጦር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና ማመቻቸት አለበት..ማለትም መለስ ዜናዊ የሱማሌን የሽግግር መሪ አብዱላሂ የሱፍን በወታደራዊ ጎይል በመርዳት ሞቃድሾ እንዳደረሰው ሁሉ..የብርሃኑን ጦር ከኋላ እየገፋ ሚኒሊክ ቤተመንግሥት አ.አበባ ለማድረስ ኢሳያስ አፈወርቂ ካለው ወታደራዊ ዝግጅትና አቅም አኳያ በተጠናከረ ምሽግ ውስጥ መሽጎ ከፊቱ የተጋረጠውን ጎይል በመጣስ ወድፊት የመግፋት ብቃቱ ከእስትራቴጂካል.ኦፐሬሽናልና.ታክቲካል ስልት አንፃር ሲታይ ችሎታ የሌለውና ደካማ ከመሆኑም በላይ ከድንበር ጀርባ እስከ መሀል አገር የሚገኘው የሕዝብ ስነ ልቦናና የከዚህ በፊቱ በወያኔ ተታሎ አንድነቱና ሉዐላዊነቱ በመደፈሩ ካገኘው ተመክሮ አንፃር በመሬታቸው ላይ የሰፈሩትን ዜጎች ጨፍልቆና ረምርሞ ወደ መሀል መዝለቅና ማለፍ ያለመቻሉ ተደምሮበት የወታደራዊ ጎይል ሚዛን የውጊያ ብቃትና ሥልታዊ እውኔታን ግምት ውስጥ ስናስገባ ብርሃኑና ወዷ አፈወርቂ ሊያታልሉንና ሊያዘናጉን ካልሆነ በስተቀር በሻቢያ ጉልበት ማነስና በድጋፍ አቅም ውስንነት ሳቢያ አዋጁ ነፃ ሊያወጣን እንደማይችል የኤርትራ ወታደራዊ ሁኔታ ስለሚጠቁም ይህም .መንገድ ቢሆን ባዶና ምንም ከመሆን አላመለጠም ከወጪ ወደ ውስጥ የማጥቃት ዘዴ .መነሻና መሽሎኪያ.የውጊያ ድጋፍና.እርዳታን ስለሚሻ ኬኒያ.ሱዳንና ጂቡቲ ክወያኔ ጋር ባላቸው ግንኙነት.ኤርትራ ጡንቻዋ ባለ መጠንከሩና ከአቅም ማነስ በመነጨ በሁሉም አጎራባች አገሮች ያለው ወቅታዊ ስዕል የሚያሳየው ለጥምር ውጊያ ትግል አመቺ አለመሆኑንና የክተት ጥሪውም የትም መድርስ አላመቻሉን ሲሆን..ሁለተኛውን የትጥቅ ትግል መንገድ በአማራጭነት ቢጠቀሙ ውጤቱ ምንሊሆን እንደሚችል ለመገመት ይረዳን ዘንድ ወደዚው ስንሸጋገር

## 2ኛ. የጦርንት አዋጁ...ከሀገር በቀል የሽምቅ ውጊያ ትግል አንፃር

ይህን..ጥራኝ ጫካው.ጥራኝ ዱሩ ብሎ ቀጣይነት ባለው መልኩ የትጥቅ ትግል የሚጀምር ሀገር በቀል ሽምቅ ተዋጊ ጎይልን መፍጠርና ሕዝብን ነፃ ማውጣት የሚቻለው እንደ ሰላማዊ ትግሉና ከዚያም በበለጠ ደረጃ ከገጠር እስከ ከተማ እንደ ቀለበት ተያይዞ በተቆራኘ አወቃቀር. በማህበራዊ.በኢኮኖሚዊ.በአራሶ አደሩ.በወጣቱ.በሴቶቸና በተለያዩ የሕብረተሰቡ ዘርፎች ውስጥ ጠንካራ ማደራጀትን..በጦር..በፖሊስና..በደህንነት ተቋማት ውስጥ ሰብሮ በመግባት ደጋፊ የማፍራት ብቃትን.የሚጠይቅ ከዘመቻ በፊት በቅድሚያ ሊረጋገጥ የሚገባው ቁልፍ ነጥብ ሲሆን. በዚህ መልኩ ተደራጅቶ ሙሁራን በአመራርና በፖለቲካው.ነጋዴው በሀብት በንብረቱ.ገበሬው.ስንቅ በማቀበል ስለ ጠላቱ..መረጃ በመስጠትና..እንቅስቃሴውን በመሰወር. በዜጎች ሁለገብ ድጋፍ ተደግፎና ታቅፎ የሚታገል ጎይል ሲሆን ከዚህ አንፃር ባልተደራጀና በሌለ ሁኔታ የታወጀው ጦርነት. ብርሃኑ ነጋ

*እራሱም የቋቋመው ድርጅትና ሠርዊቱ.በኢትዮጵያ በመሬት ላይ የሉም ከሙሁር እስከ ደቂቅ ያልተሳተፈበት.ገበሬው ቂጣ ጋግሮ ንፍሮ ቀቅሎ የማያቀብለው.ዜጎች ሁለገብ ድጋፍ ያልሰጡትና ያላቀፉት. ይህ የብርሃኑ ጦር ከየት ነው የወጣውና..የተፈጠረው..የትስ ነው ያለው? የሚለውን ጥያቄ እንዳነስ የሚያ ስገድደኝ በጎሬላ መርህ..ሀገር በቀል ሽምቅ ተዋጊ ዋናው መሰረቱ. የሀገሩ ጋራ ሸንተረርና..ጎሬላ ያለሕዝብ.አሳ ያለባሕር የሚለው መሰረታዊ መመሪያው በመሆኑ ሲሁን ከዜጎችና ከተለያዩ የህብረተሰባችን ክፍሎችና አክላት ጋር ትስስርና ቁርኝት የሌለው.ነፃ.አውጪ.እንዴት ብሎ ነፃ እንደሚያወጣን የማይታወቅ እስከ አሁን በዓለም ያልታየ አዲስ ግኝት ቢመስልም ሀ).በጥልቀትና በጥንካሬ ማደራጀትን ለ) ወደ ትግል ሜዳ መውረድን መ) በሕዝብ ውስጥ የመግባትና የመታቀፍ ችሎታን .ሲጠይቅ የነዚህ ተሟልቶ መገኘት ከእስትራቴጂክ ግብና ከታክቲክ አንፃር ወሳኝ በመሆናቸው እነዚህን በተግባር ያላዋለ አዋጅ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደምችል መገመት ሰለማያዳግትሁለተኛው አማራጭ መንገድም ያው እንደሌሎቹ ሁሉ ትልቅ ቀለበት ከመሆን አልዳነም፣*

## 3ኛ ምናልብስታዊ ግምት

*በዚህ ርዕስ ስር የማነሳቸው ሀሳቦች ምንም እንኳን ከጎሬላ አጠቃቀና ከሚታጠቀው የውጊያ ትጥቅ አንፃር ተቀባይነት የሌለው ቢሆንም እንዴትና በምን መንገድ ነፃ ሊያወጡን ይችላሉ ከሚለው ጭንቀቴ በመነሳት ምናልባት ሦስተኛው አማራጭ.ይህን የተንዛዛና አድካሚ ስራን የሚጠይቅ የድሮ ዘመን የፋራ ስልትን ወደዚያ ጥለው በሰለጠነው አካሄድና መንገድ ..የኤሌክትሮኒክ. ጦርነት መጠቀም ይችሉ ዘንድ ተሰደው ከሚገኙበት ሀገራት በትውስት ይሁን በስጦታ አህጉር አቋርጭ ተምዘግዛጊ. ቦሎስቲክና ክሩዝ ሚሳዪሎችን በመታጠቅ ካሉበት ሆነው በመተኮስ ወያኔን ሊያጠፋልን ይችላሉ ብዩ ብገምትም.ግን ይሄም ቢሆን ዝም ተብሎ ከተተኮስ ህፃን ነፍሰጡር.ሽማግሌና አዋቂ ሣይ ለይ ሕዝብን በጅምላ የሚጨርስ ትምህርት ቤት.ሆስፒታል.መገበያያ ቦታዎችንና ከተሞችን የሚያወድም በመሆኑ ይህ እንዳይሆንና ጥፋቱን መገደብ ይቻል ዘንድ የመለሰ ጦር በቆላ ደጋው በሸጦችና በተራሮች ውስጥ ተሰራጭቶ የሚያደርገውን እንቅስቃሴና ቦታ እየለዋወጠ የሚሰፍርባቸውን ወረዳዎች እየተከታተለ በመነጡብ* /location/*ኑን የሚያመለክትና እነ ብርሀኑ ካሉበት ቦታ ተኩሰው የሚልኩትን ሚሳዬል አረር /ሼል/ የሚያርፍበትን ቦታ እየተቆጣጠረና* /observe/*እያደረገ ተኩስ የሚመራና የወያኔ ጦር በተበተነበት ወረዳና አካባቢዎች ሁሉ እየተንቀሳቀሰ ሪፖርት ማስተላልፍ የሚችል ሀይል በሀገር ቤት በሕዝቡ ውስጥ ማደራጀትና መፍጠርን የሚጠይቅ በመሆኑ ይህ በሌለበት በባዶ ሁኔታ በስለጠነውም መንገድ ዘመናዊውን የኤሌክትሮኒክ ጦርነት ማካሄድ የማይቻል መሆኑን ሳስታውስ በዚህ በኩል የወሰድኩት ግምቴ የተሳሳተና አማራጭ ዕድሉም የማይሰራ መሆኑን ያረጋግጣል፣*

*ብርሀኑ ነጋና ደጋፊዎቹ መንግስት ባለ መሆናቸው በመደበኛው ሠራዊት ኅይልና የውጊያ ዘዴ መጠቀም አይችሉም. ሌለኛው የትጥቅ ትግል እስትራቴጂ በአማራጭነት የተቀመ ጠና ያለ ቢሆንም ሁለቱን ስልታዊ ክፍሎች ማለትም ጥምር የጎሬላ ውጊያንና.ሀገር በቀል የሽምቅ ትግልን ለመጠቀም ከላይ በርዕሶቻቸው ስር በተያያዥነት ባቀረብኳቸው የተግባር ድክመቶችና በአጎራባች አገሮች ባለው ወቅታዊ ሁኔታ ሳቢያ የክተት ጥሪው ከወሬና ከወረቀትነት ውጭ ወደ ተግባር መለወጥ የሚያስችል ምንም አይነት የሚታይ ስልታዊ ሥዕል የለም.፣.ግን እነዚህ ሰዎች ለትጥቅ ትግል መካሄድ አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታሰቡ ነጥቦች ሳይሟሉና ከተገቢው በላይ እያወቁና የመረዳት ብቃቱ እያላቸው ያልተደራጀና.የዶክትሪን ደሀ የሆነ አዋጅ ለምን ማወጅ አስፈለገ? .ይህ የጦርነት ጥሪ የሚያሳየው በምርጫው ማግስት ፀጥ.ረጭ አድርጎ ማንኛውንም እንቅስቃሴ በድን ሊያ ደርግ የሚችለውን በቤት ውስጥ የመቀመጥ ተቃውሞን ማክሸፍ .እስረኞችን ቤስር ቤት መከፋፈልና ዲያስፖራውን ለማፍረስ ተሞክሮ ከከሸፈው ድባ ጋር ተያያዥነት ያለው በወያኔና በባዕዳን ኅይሎች የተቀነባበረው የታላቁ ሴር አንዱ ዘርፍ ሲሆን ዋንኛው ግቡ በየወቅቱ አዳዲስ መፈክሮች እያነሱ የትኩረት አቅጣጫን ለማስለወጥ የቤት ስር በመ ስጠት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ የሚታገለው ኅይል መጠናክር እንዳይችል ከፋፍሎ ማዳከም ይቻል ዘንድ በሚገባ ተጠንቶና ታቅዶ የተጠራ ምታ ነጋሪት.ክተት ሠራዊት ነው::*

## ጦርነትን የሚፈቅደው ማን ነው?

በሰላማዊ መንገድ ለመታገል የወሰኑና የቆረጡ .ዜጎችና .የፖለቲካ ፓርቲዎች በትጥቅ ሥርዕትን መለወጥ የእምነታቸው ውጤትና ምርጫቸው ስላይደለ የጠመንጃ አመፅ እንዲ ካሄድ የሚፈቅደውና የጊዜ ሰሌዳውም ያለው በድርጅቶች ሳይሆን በጨቋኝ ገዥው እጅ ነው .የሕዝብን ጥያቄና ውሳኔ .ባለ ማክበር .የሰዎችን መብት በመርገጥ .ፍትህና ነፃነት ሲጠፋ .ዜጎች በሀገራቸው እኩል መታየትና በእኩል መኖር ሲያቅታቸው በስራ እጥነት.በበሽታ .በርሀብና. በብረት መቀጣት ሲበዛና መኖርና ያለ መኖር.ትርጉሙን ሲያጣ ተስፋ መቁረጥ የሚፈጥረው የትግል ለውጥና የትጥቅ አመፅ እንዲመጣ የሚያደርገው የአንባገነኑ ስርአት የበደል አገዛዝ ውጤት መሆኑ ቢታውቅም ያልተደራጀ ሕዝብ ለውጤት ና ለድል አይበቃማና ሰላማዊ ትግሉን እንድ አቦል ቡና አንድ ጊዜ ፉት ብለን ቀመስነው እንጂ እስከ ሦስተኛ በረካው ድረስ ስላልደጋገምነው አጠንክሮ መቀጠል አስፈላጊ ሲሆን የግፍ አገዛዝና.የብረት ማነቆው እየጠበቀ ሄዶ የሕዝቡ ሰላማዊ ትግል ወደ ትጥቅ አመፅና ሁከት እንዳይለወጥ ማድረግ ለጥያቄው መልስ መስጠትና ለውሳኔው መገዛት የሥርአቱ ሀላፍነት ሲሆን .ምናልባትም ፅዋው ሞልቶ ቢፈስ ወዳል ተፈለገ አቅጣጫና ውጤት እንዳያመራ ሁሉን ያቀፈና በሁሉም አቅጣጫ እያደራጁ በሰላማዊ ትግሉ ጠንክሮ ከመታገል ውጭ በአሁኑ ሰአት ለትግሉ ሁለተኛ አማራጭ የለም፣

ጌታመሳይ ጥላሁን
ከኖርዌይ